אמהרית

የ 17ኛው የክኔሴት ምርጫ
አስመራጭ ኮሚቴ

# በእሥራኤል የምርጫው ዘዴ

በአጠቃላይ - እድሜያቸው 18 እና ከዚያም በላይ የሆኑ የእስራኤል ዜጋ ሁሉ መሳተፍ ይችላሉ።

ሀገር አቀፍ - የምርጫው ውጤት የሚቆጠረው በሀገር አቀፍ ደረጃ ነው። ይኸውም መላው እስራኤል እንደ አንድ አካባቢ ይቆጠራል።

በቀጥታ - ተመራጮች የሚወሰኑትን በምርጫው ውጤት መሰረት ነው። (እንደ አሜሪካ የምርጫ ዘዴ ፐሬዜዳት አይደለም)

እኩል መብት -አንድ መራጭ አንድ ድምጽ አለው። እያንዳንዱ መራጭ ያለው ድምጽ ለምርጫው አንድ ነው።

ድብቅ-ምርጫው በሚስጥር ነው። ከመራጩ በስተቀር እያንዳንዱ ምን እንዲመረጡ ሌላ ሊያውቅ አይችልም በድብቅ ለመምረጥ የመረዱ መሳርያዎች አሉ እነሱም።

ሀ ፖስታው ውስጥ ያለውን የምርጫ ወረቀት የማያሳይ ልዩ ፖስታ ነው።

ለ የመረጠውን ፖስታ ውስጥ ሲያስገባ እና ፖስታውን ሲያስቀምጥ ሌላ እንዲያየው መምረጫ ክፍል።

**መራጩ ነጻ በሆነ መንገድ እንደፍላጎቱ ይመርጣሉ**

ልብ ያድርጉ ፤ ምርጫው እ.ኤ.አ መጋቢት 28.3.2006 ዓ.ም ይካሄዳል።

<u>የምርጫው ውጤት</u>

1 በምርጫው ውጤት ቢያንስ 2% ያገኘ ተወዳዳሪ ፓርቲ ከክነሴት መቀመጫ ወንበሮች መካፈል ይቻላል።

2 በትክክል በምርጫ የቀረበ ድምጾች ለ 120 የክኔሴት መቀመጫ ወንበሮች ይከፋፈላሉ።

3 እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ፓርቲ የሚያገኘው ድምጽ መሰረት የክኔሴት አባላቱ ቁጥር ይወሰናል።

<u>የምርጫ ካርድ ምን ነው</u>

የምርጫ ካርድ የመመረጥ መብት ያላቸውን የሚያሳውቅ ነው።

የመምረጥ መብት የሚሰጥ የምርጫ ካርድ ላለው ብቻ ነው።

የመምረጥ መብት የሚሰጠው ከዚህ በታች የሚዘረዘሩ ሶስት ነጥቦችን የሚያሟሉ ናቸው።

ሀ እስከ 2.2.2006 ዓ.ም ድረስ የእስራኤል ዜጋ የሆነ

ለ ከ 28.3.1988 ዓ.ም በፊት የተወለደ

ሐ ከ 8.2.2006 ዓ.ም በፊት ስሙና አድራሻው በሀገር አስተዳደር ሚ\ጽቤት የህዝብ ቁጥር የተመዘገበ።

ለመራጮች መምረጫ ካርድ የሚመረጥበትን ቦታ ለማወቅ
ከ 6.2.06 አም አንስቶ እስከ 18.3.06 በኢንተርኔት በይፋ ይሆናል።

<u>የት ነው የሚመርጡት?</u>

- የአስመራጭ ኮሞቴው ከምርጫው ጥቂት ቀናት አስቀድሞ የስልክ መስመር ይዘረጋል። የስልክ ቁጥሮች በጋዜጣ በይፋ ይነገራል።

- ለአካለ ስንኩላን ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ለማይችሉ አመች የሆነ የመምረጫ ቦታ ይዘጋጅላቸዋል። በአስመራጭ ኮሚቴው ጣቢያ ደውሉ የት መምረጥ እንደሚቻል መጠየቅ ያስፈልጋል። ምርጫውም በድርብ ፖስታ ይሆናል።

- በአዛ ስር እና በሰሜን ሰማርያ የነበሩ ይሁዳውያን በኒጻኒ እና በተለያዩ ቦታዎች በሚያመቻቸው መምረጥ ይችላሉ።

- ሆስፒታል የሚገኙ ህሙማን ፥ በእስር ቤት ፥ ለመርከበኞች ፥ በውጭ ሀገር ለሚገኙ የእስራኤል መንግስታት ሰራተኞች ባሉበት መምረጥ ይችላሉ።

## אמהרית

- ለምርጫው ሶስት ሳምንታት ሲቀሩ ለመራጮች የሚመርጡበትን ቦታና አድራሻ በፖስታ ይላካል የመምረጫ ቦታ ካርታ በኢንተርኔት www.gov.il ማግኘት ይቻላል።

## የምርጫ ቀን

የምርጫ ቀን የእረፍት ቀን ነው። የህዝብ ማጓጓዣወች ግን ይሰራሉ ። የምርጫ ጣቢያዎች የሚከፈቱት ከጥዋቱ 7 ሰአት እስከ ምሽቱ 10 ድረስ ነው። አነስተኛ በሆነ መንደሮች የነዋሪዎችን ቁጥር ከ 350 የማይበልጥ ከሆነ የምርጫ ጣቢያዎች የሚከፈቱት ከጥዋት 8 ሰአት እስከ ምሽቱ 8 ሰአት ድረስ ነው። አስቀድመው ከምርጫ ጣብያ ደርሰው ነገር ግን በተራ ብዛት ከዘገዩ መምረጥ ይቻላል። የምርጫው ሰአት ከተዘጋ በኋላ የሚመጡ ግን መምረጥ አይችሉም።

ለምርጫው ከዚህ በታች ከሚከተሉት መታወቅያዎች አንዱን ይዘው መቅረብ አለብዎት።

- ትኡዳ ዘሁት ፎቶ ግራፍ ያለበት።
- የእስራኤል ፓስፖርት ጊዜው ያላለፈበት ፎቶ ግራፍ ያለበት።
- የመንጃ ፍቃድ ጊዜ ያለፈበት ፎቶ ግራፍ ያለው።
- የክኔሴት አባል መታወቅያ።

## የምርጫ ወረቀት እና ጣብያ

የሚከተሉት ሂደቶች

ሀ መራጭ ከምርጫው ጣቢያ እንደደረሰ ከአስመራጭ ኮሚቴው ፊት በመቅረብ መታወቅያ ያሳያል።

ለ ስሙ በመራጭ ስም ዝርዝር እንደተገኘ ሰማያዊ ፖስታ ከላዩ ላይ 17ኛው የክነሴት ምርጫ የሚል ጽሁፍ ያለው ይቀበላል።
ፖስታውም ተዘግቶ ለአስመራጮች ሃላፊነት ካላቸው ፊት ለፊት ይሆናል።

ሐ መላው መራጭ ወደ መምረጫው ክፍል ገብቶ በውስጥ የተወዳዳወች ዝርዝር ያለበት ነጭ ንጹህ ወረቀቶች ያገኛል።

## ለክኔሰት ምርቻ ወረቀቶች ለእያንዳንዱ ተወዳድሪ

ምርጫው ለተወዳዳሪዎች ዝርዝር ነው።
በምርጫው ወረቀት የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ምልክት ፊደሉ ወይም ቃል ተጽፎባቸዋል ምልክቶች አስቀድሞ በጋዜጦች ይፋ ይወጣል።

ምርጫው የሚካሄደው፤

ሀ መራጩ አንድ ወረቀት ብቻ ይመርጣል ይኸውም የሚፈልገውን ተወዳዳሪ ይሆናል። ወረቀቷን ፖስታ ውስጥ ያሸገዋል ያስገባል መራጩ ነጭ ወረቀት መጠቀም ይችላል። ከምርጫ ወረቀቶች አጠገብ ስለሚገኝ ነጭ ወረቀት በመውሰድ በእጅ ጽሁፍ (በእብራይስጥ ወይም በአረብኛ) የሚመርጡትን ፓርቲ ምልክት ወይም ፊደል መጻፍ ይችላል።

ለ መራጩ ፖስታውን ካሸገ በኋላ ከአስመራጭ ኮሚቴው ፊት በመቅረብ ከመምረጫው ሳጥን ውስጥ በእጅ ራሱ ያስገባዋል።

ሐ መራጩ በቦታው የሚገኙ ስነስርአት የሚያስከብሩ የሚሰጡትን መመሪያ ማሟላት አለበት።

በፖስታ ውስጥ ማስገባት በሚፈቀደው አንድ ወረቀት ብቻ ነው። ከአንድ ወረቀት በላይ የተለያዩ ምልክ ከተገኘ (እንደ አንድ ድምጽ ብቻ ነው የሚቆጠረው) ነገር ግን ከሁለት የበለጠ ተመሳሳይ ካርድ ከፖስታው ከተገኘ ወይም ለሌላ የሚሆ ን ምርጫ ከተገኘ የመረጠው እንዳልመረጠ ይቆጠራል።

መግለጫ በእብራይስጥ ቋንቋ አርጅናሉ ፤ ከጠበቃ አየሌት ፊሽማን አጠቃላይ አስመራጭ ኮሚቴ ምክትል ሀላፊ ሚስራድ ሀፒኒም
www.gov.il

አምአርኛ፣ እንዲተረጎም የተባበረው የቅሊጣ መስርያ ቤት የማስታወቅያ ክፍል ነው።
www.moia.gov.il

መብቱ 2006 ዓ.ም እየሩሳሌም የተጠበቀ ነው።